በመላው ዓለም ለምትኖሩ ኢትዮጵያውያን በሙሉ

የአገራችንን ምስቅልቅል ፖለቲካ ለማስተካከልና በሕዝባችን ላይ የተፈራረቀውን የአምባ ገነኖች አገዛዝ አስወግዶ በምትኩ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማስፈን ብዙ ተጋድሎ ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ሕዝባችን በአምባገነኖች በትር ሳይበገር ፡ በገዛ ድርጅቶቹ የውስጥ ክፍፍልና ፡ የድርጅቶች በአንድነት ያለመቆም ችግር ትግላችንን እያዳከመው ዛሬም ሕዝባችን እየከፈለ ያለውን መስዋዕትነት ሳያንሰው ፡ ነፃነቱ ግን እየራቀው ነው፡፡

የዴሞክራት ኃይላት መተባበር በትግሉ ላይ ያለውን አዎንታዊ አስተዋጽዖ በግንቦት 1997 በተደረገው ምርጫ አይተነው ነበር፡፡ ግና ፡ ብዙ መስዋዕትነት ተከፍሎበት ነፃነት ዋዜማ ላይ የደረሰው ትግል ፡ ያው እንደተለመደው ፡ የመከፋፈል እና በአንድ ያለመቆም ችግራችን አገርሽቶበት ፡ የሕዝባችን ድል ሊነጠቅ አፋፍ ላይ መድረሱ ዛሬም አሳሳቢ ጉዳይ ሆኗል፡፡

የመለስ አገዛዝ ላለፉት አስራ ስድስተ ዓመታት ደብዛቸውን አጥፍቶ የሰወራቸውን የሕዝብ ወገኖች ፡ ከዚያም ወዲህ እነ አበራ የማነ አብንና የአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ተማሪዎች ሌሎችም በብዙ በሺህ የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞች ፡ የግንቦቱን ምርጫ ተከትሎም በእንበለ ፍርድ ያሰራቸውን የቅንጅት መሪዎች ፡ የነፃ ጋዜጠው ማኅበረሰብ እና የሲቪክ ማኅበራት አባላት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ  እንዲፈቱ በጋራ መቆም ነበረብን፡፡ ይሁን እንጂ በአንድነት የመቆማችን ኹኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ ተስፋ የሚያስቆርጥ ደረጃ ላይ ደረሷል፡፡

ይህ የመበታተን አደጋ ካሳሰባቸው ወገኖች መካከል ፡ በተለያዩ ድረ ገጾች የውይይት መድረክ ከፍተን የአቅማችንን አስተዋፅዖ በማድረግ ላይ ያለን የፓልቶክ ስብስቦች ልዩነትን ያስወገደ *አንድነት ለፍትህ በሚል የታሰሩት የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ* ስንል የሻማ ማብራት ሥነ ስርዓት አዘጋጅተናል፡፡

ይሻማ ማብራቱ ሥነ ስርዓት የመለስ አገዛዝ በፍርድ ስም እያንገላታቸው ያሉትን የቅንጅት መሪዎች የጋዜጠኞችና የሲቪክ ማህበራት አባላት ለፍርድ የቀጠረበትን ማረች 5 አስታኮ ከወዲሁ ሐሙስ ማርች 1 2007 በመላው ዓለም ይካሄዳል፡፡ በዚህም ዝግጅት በርካታ የሲቪክ ማሕበራት ይሳተፋሉ፡ መልዕክቶቻቸውንም ያደርሳሉ፡፡

የተከበራችሁ ወገኖቻችን ዐለም አቀፉ ማኅበረሰብ በሕዝባችን ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍና መከራ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ድጋፉን ለመለስ አገዛዝ መቀጠሉን ለመቃወምና ፡ የአንድነታችንን መንፈስ ለማነጽ በፖለቲካ ፣ በኃይማኖት ፣ በዘርና በጎሳ ሳንለያይ የፊታችን ሐሙስ ማርች 1 2007 በመላው ዓለም በአንድነት ለፍትሕ ምሽት ላይ ተገኝተን ድምጹን ለተነፈገው ወገናችን ድምጻችንን ከፍ አድርገን እንድናሰማ በታላቅ አክብሮት ጥያችንን እናቀርባለን፡፡

አስተባባሪዎች፡

- Ethiopian Diaspora disscussion Forum room
- Ethio Current event Assimba disscussion room
- Ethiopian Struggel for Freedom and Democracy room
- Kinijit Discussion Forum room

participating  Civic Orgnaizations will be disclose soon.